# በህልሞችዎ ይመኑ።
# እኛ እናምንበችዋለን።



# ህልምዎን ወደ እውነታ ይቀይሩ

ትልልቅ ህልሞች እንዳላችሁ እና ከግብ ለማድረስ በርትታችሁ እየሰራችሁ እንደሆነ እናውቃለን። ከሁለተኛ ደረጃ በኋላ ስለሚኖራችሁ ህይወት ስታስቡ፣ እነዚያ ህልሞች እውን ሊሆኑ ወደሚችሉበት፣ ስለ University of Washington እንዲያውቁ እንጋብዛችኋለን።

የብዝሃ ባህል ማሰራጫ እና ምልመላ (MOR Multicultural Outreach & Recruitment) ቡድን የእርስዎ አጋር እና ትልቅ ደጋፊ ለመሆን እዚህ ተገኝቷል። ከኛ የ MOR የቅበላ አማካሪዎች ጋር ዛሬውኑ ይገናኙ። ስለ ማመልከቻው ሂደት፣ የገንዘብ ድጋፍ እና ከዚያም ባሻገር ጥያቄዎችን ለመመለስ ዝግጁ ናቸው። እናም አንዴ በይፋ ሀስኪ ከሆኑ፣ የአናሳ ጉዳዮች እና ብዝሃነት ቢሮ እስከ ምርቃትዎ ድረስ፣ በእርስዎ ስኬት ላይ ያተኩራል።

ስለ የእርስዎ የወደፊት ጊዜ በጣም ደስተኞች ነን — እና UW የጉዞዎ አካል እንዲሆን ለማድረግ ጓግተናል። ይቀላቀሉን።

W

UNIVERSITY *of* WASHINGTON

# MULTICULTURAL OUTREACH & RECRUITMENT

Office of Minority Affairs & Diversity


University of Washington
Multicultural Outreach & Recruitment
Box 355845
Seattle, WA 98195

(206) 221-6463

reach@uw.edu

depts.washington.edu/reach

@uwmor

@uwomadmor

@uwmor





Favian Mares, ’22
Toppenish, WA
ትምህርት፣ ማህበረሰቦች እና ተቋማት

# ለማለም ይድፈሩ

## ኮሌጅን የቀለለ እናድርግ

ገና አሁን ልያስቡበት ቢጀምሩም ወይም ህልምዎ የሆነውን ኮሌጅ ቀድመው ያገኙ ቢሆንም፣ ያንን ማድረግ የተወሳሰበ እንደሆነ ይገባናል። ስለዚህ እኛ ቃል የምንገባልዎ ይህንን ነው፦ በጉዞዎ ላይ በየትኛውም ቦታ ላይ ቢሆኑ፣ እኛ ከግብዎ እንዲደርሱ እንመራዎታለን። በ UW ውስጥ አካል ነዎት — እንዲሁም እኛ እዚ እንዲመጡ እንፈልጋለን።

## UW ለእርስዎ ነው

ከ Puget Sound እስከ Spokane፣ ከ Bellingham እስከ Walla Walla እና ባሻገር፣ UW ለሁሉም ዋሽንግተናውያን በመሆኑ ኩራት ይሰማዋል። በ 2020፣ ከዝቅተኛ ውክልና ካላቸው ማህበረሰቦች በታሪካችን ትልቁን የመጀመሪያ ዓመት ተማሪዎች ቁጥር ተቀብለናል — በቤተሰባቸው ውስጥ የመጀመሪያዎቹ የአራት-ዓመት ኮሌጅ ተማሪ የሆኑትን ጨምሮ። የእኛ ግዞፍ፣ ቅይጥ የሀስኪ ቤተሰብ ለእርስዎ ቦታ አለው።

**29%**

በ UW ውስጥ ካሉ ሀስኪዎች የመጀመሪያ ትውልድ የኮሌጅ ተማሪዎች ናቸው።

**70%**

ከ UW ተማሪዎች ከተመረቁ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ስራ ይቀጠራሉ።

W

## ለማጠቃለል ያክል

የእኛ ድጋፍ የይቀላቀሉን ጥያቄዎን ሲያገኙ የሚያበቃ አይደለም። ዝቅተኛ ውክልና ካላቸው ቡድኖች በዋሽንግተን ውስጥ ካሉ ሌሎች የአራት-ዓመት የህዝብ ተቋማት ይልቅ ብዙ ተማሪዎች በሲያትል ከሚገኘው UW ካምፓስ ይመረቃሉ። በዓለም ላይ ለውጥ ለማምጣት ሙያዎን ሲጀምሩ በማየታችን፣ በጣም ተደስተናል፣ እና ጠንካራ ስራዎ ውጤታማ እንዲሆን ማረጋገጥ እንፈልጋለን።

*ዝቅተኛ ውክልና ያላቸው ቡድኖች ቀለም ያላቸው ተማሪዎችን (የአሜሪካ ህንዳዊ/የአላስካ ተወላጅ፣ ጥቁር/አፍሪካዊ አሜሪካዊ፣ እስፒናዊ/ላቲን፣ የሃዋይ ተወላጅ/የፓሲፊክ ደሴት ተወላጅ እና ደቡብ ምስራቅ እስያ) እንዲሁም በታሪክ ከከፍተኛ ትምህርት መብት የተነፈጉ ቡድኖች ተማሪዎችን ያካትታል።*

**"በካምፓስ ውስጥ ብዙ አናሳ-ማህበረሰቦች አሉ። UW በሚሰጣቸው የመርሃ ግብር ዓይነቶች የተነሳ የእኔን በአስደናቂ ፍጥነት በማግኘቴ እድለኛ ነኝ፣ ስለዚህ አስቀድሜ የማውቃቸው ሰዎች ነበሩ።"**



Mahilet Abraha, ’23
Shoreline, WA
የሰው ሃብት አስተዳደር እና
የመረጃ ስርዓቶች

UNIVERSITY *of* WASHINGTON
MULTICULTURAL OUTREACH & RECRUITMENT
**Office of Minority Affairs & Diversity**

# የሚቻል ነገር እናድርገው

## የገንዘብ ወሬ

**አፈታሪክ፦** ነጻ የትምህርት እድሎች ለከፍተኛ ውጤት ያላቸው ተማሪዎች እና አትሌቶች ብቻ ነው።

**እውነታ፦** UW የማዕረግ ተመራቂዎችን እና የኮሌጁ አትሌቶችን በደስታ ይቀበላል — ነገር ግን ለሁሉም ተማሪዎች የነጻ የትምህርት እድል እና ፍቃዶች አሉን።

**ተረት፦** ወደ ኮሌጅ መግባት ማለት ብዙ የተማሪ ብድሮችን መሰብሰብ ማለት ነው።

**እውነታ፦** የ UW ተማሪዎች ከብሔራዊ አማካዩ ባነሰ እዳ — እንዲሁም የ UW ቅድመ ምረቃዎች 63% ያለ ምንም እዳ ይመረቃሉ።

ለኮሌጅ መክፈል በጣም ውድ ነገር ሊሆን አይገባም። ለስራ- ትምህርት ቦታዎች ከነጻ የትምህርት እድሎች እና ፍቃዶች ብዙ አማራጮች አሉ። የእራስዎን ትምህርት ወጪ እንዲሸፍኑ እና ባነሰ እዳ እንዲመረቁ፣ የእኛ የገንዘብ ድጋፍ አማካሪዎች እርስዎን እና ቤተሰብዎችዎን በሂደቱ ዙሪያ ያስጎበኙዎታል።

**$400** ሚልዮን
በገንዘብ ድጋፍ
በየዓመቱ የሚሰጥ

**#1** ኮሌጅ
አብዛኛውን ክፍያ
የሚከፍል

(CNBC Make It)

## የእኛ የሀስኪ ቃለ መሀላ

የሀስኪ ቃልኪዳን ለዋሽንግተን ስቴት ተማሪዎች ዋስትናችን ነው፡ የ UW ዲግሪን ለማግኘት የገንዘብ ችግሮች እንቅፋት እንዲሆኑ አንፈቅድም። ለሀስኪ ቃልኪዳን ብቁ ከሆኑ፣ የእርስዎ ትምህርት እና ክፍያዎች ሙሉ በሙሉ (አዎ ልክ ነው — ሙሉ በሙሉ የተሸፈኑ!) ለአራት ዓመታት የተሸፈኑ ይሆናሉ። በየዓመቱ፣ ምስጋና ለሀስኪ ቃልኪዳን ይሁንና፣ ወደ 10,000 የዋሽንግተን ተማሪዎች የሚጠጉ ለ UW ምንም ዓይነት የትምህርት ክፍያ አይከፍሉም። ይሄ እርስዎ ሊሆኑ ይችላሉ።

የበለጠ መረጃ ያግኙ፡- **uw.edu/huskypromise**



Jordan Crawford (Kuskokwim), ’21
Black Diamond, WA
የንግድ አስተዳደር (ማርኬቲንግ)

> “ከሀስኪ ቃልኪዳን እና ብዙ ፍቃዶች ጋር የ Costco ብዝሃነት ነጻ የትምህርት እድል ተቀባይ ነበርኩ። እነዚህ ግብዓቶች በ UW የመገኛት ወጪዎቼን ሸፍነውልኛል — ከእጅ ወደ አፍ ኑሮ ከሚኖር ቤተሰብ በመምጣቴ የማይታሰብ ነገር ነው።”

UNIVERSITY of WASHINGTON
MULTICULTURAL OUTREACH & RECRUITMENT
Office of Minority Affairs & Diversity

# ቤተሰብዎን ያግኙ

## እርስዎ አካል የሆኑበት ቦታ

UW ቦታ ብቻ አይደለም፣ አንድ ቤተሰብ ነው። የእርስዎን ዓይነት ሰዎች ከ 1000 በላይ በሆኑት የተማሪ ክበቦች ውስጥ ሊያገኙ ይችላሉ — ከባህላዊ ተቋማት እስከ የግሪክ ሕይወት፣ ከቀስት እስከ አካፔላ ይገኙበታል። ፍላጎትዎን የሚያነሳሳው ምንም ይሁን ምን፣ የእርስዎን ስሜት የሚጋሩ ሌሎች ሰዎች የማግኘት እድልዎ የሰፋ ነው።

## ሁለተኛው ቤትዎ

የ UW ካምፓስ ማህበረሰብ ነው — እና ከቤት ቢርቁም ቤትዎ ነው። በካምፓስ ዙርያ፣ ከመኖሪያ አዳራሾች እስከ Samuel E. Kelly Ethnic Cultural Center (በሀገሪቱ ውስጥ ትልቁ የኮሌጅ የባህል ማዕከል) ድረስ እንግዳ ተቀባይ ቦታዎችን የሚያገኙ ሲሆን **wəɫəbʔaltxʷ** – Intellectual House፣ ለአሜሪካ ህንዶች እና የአላስካ ተወላጆች በረጅም የቤት አይነት የተሰራ የመሰብሰቢያ ቦታንም ያካትታል።

## ከበስተጀርባዎ ያለ ማህበረሰብ

በ UW ለብቻዎ አይሆኑም። እዚ ከመድረስዎ አስቀድሞ ራሱ፣ በእርስዎ ጫማዎ ውስጥ መሆን ምን እንደሚመስል በሚያውቁ አማካሪዎች መተማመን ይችላሉ። የአናሳ ጉዳዮች እና ብዝሃነት ቢሮ እና የብዝሃ ባህል ማሰራጫ እና ምልመላ ቡድን ሁሉም ሰው ሊሳካለት የሚችልበትን የተለያዩ፣ ሁሉን ያካተተ ካምፓስ ለመፍጠር መስራት።

## የተማሪዎች እና የባህል ተቋማት የሚከተሉትን ያካትታሉ፦

የጥቁር ተማሪዎች ህብረት

የአካል ጉዳተኝነት ተሟጋች ተማሪዎች ህብረት

የፊሊፒን አሜሪካዊ የተማሪዎች ህብረት

የመጀመሪያ ሀገራት በ UW

የክመር ተማሪዎች ህብረት

MEChA de UW

ፖሊኔስያውያን የተማሪዎች ህብረት

ወይንጠጅ ቡድን

የተለዩ የቀለም ሰዎች ህብረት

… እና ሌሎችም!

"ብዙ ባልደረቦች ነጭ እንደሆኑ በማየቴ እና የነጭ ተቋማት ላይ መኖር የማይገባኝ ቦታ ነው ብዬ ጨንቆኝ ነበር። ምቾቱ የመጣው ብቻዬን እንደማልሆን ካወቅሁ በኋላ፣ ዝቅተኛ ውክልና ያላቸውን፣ የመጀመሪያን ትውልድ ተማሪዎች የሚደግፉ እንደ የአናሳ ጉዳዮች እና ብዝሃነት ቢሮ አይነት ሌሎች ቢሮዎችን ሳስተውል ነው።"



Ammara Touch, ’21
Kent, WA
ባዮሎጂ እና አሜሪካዊ የዘር ጥናቶች

UNIVERSITY of WASHINGTON
MULTICULTURAL OUTREACH & RECRUITMENT
Office of Minority Affairs & Diversity

UNIVERSITY of WASHINGTON
MULTICULTURAL OUTREACH & RECRUITMENT
Office of Minority Affairs & Diversity

UNIVERSITY of WASHINGTON
MULTICULTURAL OUTREACH & RECRUITMENT
BOX #355845
SEATTLE, WA 98195

FIRST LAST NAME
ADDRESS LINE 1
ADDRESS LINE 2
CITY, STATE ZIP



